# ራሱን የማይሸፍነው ሽፋን …

ቴዎድሮስ በላይ (ከካሳንቺስ)

በቅርቡ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን "የግሉ ፕሬስ ውልደትና እድገት" በሚል ርዕስ ኢትዮጵያ ውስጥ የነፃ ፕሬስ ከተፈቀደ በኋላ ባሉት አስራ ስምንት ዓመታት የነበረውን የግል ጋዜጦች ገፅታና አካሄድ አስታውሶናል፡፡ ይህን ተከትሎ የተለያዩ የግል ጋዜጦች የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ባቀረበው ፕሮግራም ላይ የዜጐችን፣ የጋዜጠኞችንና የፖለቲከኞችን አስተያዬት ያካተቱ ዜናዎችንና ሃተታዎችን አቅርበውልናል፡፡ ከእነዚህ ጋዜጦች መሀከል አርብ ታህሣሥ 9 ቀን 2002 ዓ.ም የወጡት የነጋድራስና የነገል ጋዜጦች እንዲሁም የቅዳሜ ታህሣሥ 10 የአዲስ አድማስ ጋዜጦች ዕትሞች ይገኙበታል፡፡

ጐግል "ኢቲቪ የግል ፕሬስ ላይ ባቀረበው ትችት "ከህዝብ አስተያየት" በሚል ርዕስ የሁለት ጋዜጠኞችንና የስድስት የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎችን አስተያየት አስነብቦናል፡፡ በእኔ እምነት ጋዜጦቹ ሰሞነኛ በሆነ አገራዊ ጉዳይ ላይ የህዝብን፣ የባለሙያዎችንና የፖለቲከኞችን አስተያየት ጠቅሶ ዘገባዎችን ማቅረባቸው አስፈላጊና ተገቢ ነው፡፡ ይሁን እንጂ መላው ሕዝብና ባለሙያዎች በሙሉ በጉዳዩ ላይ ተመሳሳይ አመለካከት ያላቸው ይመስል የአንድ ወገን አመለካከቶችን ብቻ ማቅረብ ከጋዜጠኝነት የሙያ ሥነ–ምግባር ጋር ግጭትን ማስከተሉ አይቀርም፡፡ በተለይ ሁሉንም አመለካከቶች ከወገናዊነት ውጭ እንደያስተናግድ በሚጠበቅ ነፃ የግል ሚዲያ ሲቀርብ፡፡ ነጋድራስ ጋዜጣ "የኢቲቪ ፕሮግራም ለጋዜጠኞችና በባለሙያዎች አስተያየት" በሚል ርዕስ በጉዳዩ ላይ የፊት ገፅ ዜናውን አስነብቦናል፡፡ የአዲስ አድማስ ጋዜጣም ፖለቲከኞችን ጠቅሶ የዜና ዘገባ ከማቅረቡም በላይ በውስጥ አምዶቹ ላይ በጉዳዩ ዙሪያ አስተያየቶችን ይዞ ወጥቷል፡፡

እንደዜጋ እኔም በጉዳዩ ላይ የራሴ አስተያየት ስላለኝ እነዚህ ጋዜጦች ላይ ከቀረቡት ለግል እይታዬ ቅርፅ ያሰጡልኛል ያልኳቸውን በመነሻነት ጠቅሼ አስተያየት ለማቅረብ ወድጃለሁ፡፡

በጉዳዩ ላይ አስተያዬታቸውን የሰነዘሩ የተቃዋሚ ፖለቲከኞችን በተመለከተ ብዙም መናገር ያለብኝ አይመስለኝም፡፡ በኢቲቪ ፕሮግራም የተላለፉ የመጥፎ ዘገባ ናሙናዎች ላይ የሰፈሩ እጅግ አሳፋሪ ኢ– ዴሞክራሲያዊና ፀረ –ፕሬስ ፅሁፎችና ንግግሮች ባለቤቶች በመሆናቸው በወንጀል ተጠያቂ የነበሩና የተቀጡ፣ ለቅጣት ባይዳረጉም እንኳ ከሞራል ተጠያቂነት በማያመልጡ ፖለቲከኞች የተሰጡ አስተያዬቶች ነበሩ ፡፡ አስተያዬቶቹ ሚዛናዊ ይሆናሉ ብሎ መጠበቅ የዋህነት ይመስለኛል፡፡ ፕሮግራሙን ፀረ – ፕሬስ ፕሮፓጋንዳ በማለት ያዋደቁት እነዚህ ግለሰቦች የሰጡት አስተያዬት

የቀድሞው ተግባራቸውን አስመለክቶ ተፀፀች ህሊና የሌላቸው መሆናቸውን ከማሳየት ያለፈ ፋይዳ ያለው ነገር ተናግረዋል አልልም፡፡

በነገል ታህሣሥ 9፣ 2002 ዕትም ላይ ከቀረቡት 8 አስተያየት ሠጪዎች መካከል ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በጋዜጠኝነት የተመረቁት ጋዜጠኛ ዘላለም እና የሣራን አስተያየት፣ ከነጋድራስ ዜና ላይ ደግሞ የአዲስ አድማስን ከፍተኛ አዘጋጅ  አቶ ሰለሞን ገ/እግዚአብሔር የሠጡትንና እንዲሁም አዲስ አድማስ ከጠቀሣቸው የተቃዋሚ ፖለቲከኞች አስተያዬትም የተወሰኑትን እጠቅሳለሁ፡፡

ጐግል የጠቀሳቸው ጋዜጠኛ ዘላለም የግሉን ፕሬስ በተመለከተ ከኢቲቪ ፕሮግራም ሁለት ነገሮችን እንደተገነዘቡ ገልፀው ፣ "በምርጫ 97 አካባቢና ከዚያ በፊት የነበሩት ጋዜጦች ሙሉ በሙሉ ከሙያ መርሕ ውጭ አድሏዊ እንደነበሩና በአሁኑ ሰዓት ደግሞ ምርጫ 2002 እየተቃረበ ሲመጣ መንግስት ነፃ ፕሬሱ ላይ ያለውን ሽምቀቅ እያጠበቀ" መጥቷል ብለውናል፡፡ ጋዜጠኛው ማብራሪያቸውን በመቀጠል በምርጫ 97 አካባቢ የነበሩ ጋዜጦች የተለያዩ ድርጅቶች ልሣን እንደነበሩና የአሁኖቹ ግን የኢህአዴግ ደጋፊዎች የሆኑ ጭምር እንደሚያነቧቸው ገልፀው፣ " እንደዚህ ዓይነት ፕሮግራም በቴሌቪዥን መተላለፉ በራሱ የግል ፕሬስን የሚያሸማቅቅ ዛቻ ነው፡፡" በማለት አስተያየታቸውን  አጠቃለዋል፡፡

በምርጫ 97 አካባቢ፣ ከምርጫው በፊትና በተለይም ከምርጫው በኋላ ይሠራጩ የነበሩ አብዛኞቹ የግል ጋዜጦችን የድርጅት ልሣን መሆናቸውን በተመለከተ ከፕሮግራሙ ያገኙትን ግንዛቤ ብዙዎች ይጋሩታል፡፡ የአሁኖቹ ጋዜጦች የኢህአዴግ ደጋፊዎችም የሚያነቡዋቸው / የቀድሞዎቹን ያነቡ እንደነበር ሳይዘነጋ በመሆናቸው የኢቲቪ ፕሮግራም መንግሥት የነፃ ፕሬሱ ላይ ሽምቀቆውን እያጠበቀ መምጣቱን፣ የግል ፕሬሱን የሚያሸማቅቅ ዛቻ…. መሆኑን አስገንዝቦኛል የሚለው የዘላለም አስተያየት ግን፣ ከአንደኛው ግንዛቤው ጋራ የሚጣረስና ምርጫ 97 አካባቢ የነበረውን የጋዜጦች አካሄድ ባለማወቅ፣ ወይም በመዘንጋት የተሰጠ አምታች አስተያዬት ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡አቶ  ዘላለም እንዳሉት፣ የኢቴቪው ፕሮግራም ምርጫ 97 አካባቢ የነበረውን የግል ጋዜጦች ሁኔታ እንዲገነዘቡ ካደረጋቸው ከምርጫ 97 በኋላ ለተፈጠረው ቀውስ አስተዋፅኦ ማድረጋቸውንም መገንዘብ ነበረባቸው ፡፡ በወቅቱ ቀደም ሲል የመዝናኛ ኪነጥበብ፣ ፍቅር ላይ የሚያተኩር ፖሊሲ የነበራቸው ጭምር የተቀሩት ጋዜጦች የፈጠሩትን መሠረት ቢስና የህዝቡን ግንዛቤ ያዛቡ ዘገባዎችን የመንዛት ልክፍት ተጋብቶባቸው፣ እንደነበር ሲታይ ደግሞ በወቅቱ ጋዜጦቹ ያሳዩትን ድንገተኛ አሉታዊ የአካሄድ ለውጥ ያስታውሳል፡፡ ይህ ከሆነ በኢቲቪ የቀረበው ፕሮግራም የግል ጋዜጦችን የሚያሸማቅቅ ዛቻ ከመሆኑ ይልቅ ለተመለከተው ከ97 ምርጫ በሁዋላ በአገርና በህዝብ ላይ የደረሰውን ጉዳት በማሳየት ካለፈው ትምህርት በመውሰድ ረብሻና አመፅ የሚያነሳሳ ኢ– ማህበራዊና ኢ– ሙያዊ አሰራር እንዳይከተሉ ለማሳሰብ መሞከር ህብረተሰቡም ቢሆን ካለፈው መጥፎ ተሞክሮ ልምድ ቀስሞ ከመሰረታዊ የሙያ መርሆዎች ያፈነገጡ ህትመቶችን ሳያላምጥ መዋጥ የሌለበት መሆኑን በማሳወቅ ህገወጥ አመፅ ውስጥ እንዳይዘፈቁ ለማስታወስና ለማሳሰብ የተሰጠ መሆኑ

ያይላል። አሁን ያሉ ጋዜጦች አቶ ዘላለም እንዳሉት ነፃና ገለልተኛ ከሆኑና በዚሁ አካሄድ እንደሚቀጥሉ እርግጠኛ ከሆኑ ደግሞ፣ የሚያሸማቅቃቸው አንዳችም ነገር የለም። ነገሩ "ምን ያለበት ምን አይችልም" እንደሚሉት ካልሆነ በስተቀር ። በመሆኑም በእኔ እምነት ይህ የአቶ ዘላለም አስተያየት ነፃ ፕሬስ ለሰላምና ለዴሞክራሲ መጎልበት ያለውን ሚና ከሚያውቅ ወይም ያውቃል ተብሎ ለሚታሰብ ጋዜጠኛ የሚመጥን ሆኖ አላገኘሁትም።

ሌላው ከጐግል ጋዜጣ ልጠቅስ የፈለጉት ሣራ የተባሉ አስተያየት ሠጪን ሃሳብ ነው። ሣራ ስለፕሮግራሙ የተሰማቸውን ሲገልፁ "አነግ ውጊያውን አፋፍሞታል፣ የመለስ ሣጥናኤላዊ የዙፋን አስተዳደር ለመጨረሻ ጊዜ መውደም አለበት፣ የትግራዩን ገዥ ፓርቲ ለመጣል ትግራይ በቀል ፓርቲ ተደራጀ፣ ወያኔ ተደናበረች፣ ተናወጠች" በሚል መፈክር መሰል የዜና ርዕስ (በቃለ አጋኖ ምልክት የታጀቡም አሉበት) ርዕሰ እየጮሁ የቀረቡ ዜናዎችና እንዲሁም ውዳሴ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም አስተያየቶቹ ለገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ አደገኛ ናቸው ነበር ያሉት። ሣራ ምን ለማለት እንደፈለጉ በግልፅ ባይታወቅም "በአሁኑ ወቅት ከብሔረሰብ ቁጥር አኳያ በአንድ ብሔር ላይ የተካሄደ ጭፍጨፋ፣ የመገንጠልና ያለመገንጠል ጉዳዮች አሁንም ድረስ በቋፍ ላይ ባሉበት ሁኔታ "በአዲስአበባ ወሕኒ ቤት ኦሮሚፋ መናገር ተከለከለ፣ ትግራዮች ከመገንጠል ወደ ኋላ እንደማይሉ አስጠነቀቁ፣ አሕዴድ እንደአባቱ ኢሕአዴግ አማራው ላይ ዘመተ" በማለት ለተመልካች መልሦ መንገር አንዱ በሌላው ላይ እንዲነሳ የተላለፈ ጥሪ ያስመስለዋል።" በማለት ፕሮግራሙ የአንዳንዶች ድብቅ አላማ ሳይሆን አይቀርም የሚል ስጋት እንዳላቸው ገልፀዋል።

ሣራ ሕዝብን በሕዝብ ላይ የሚያስነሳ ችግር እንዳይፈጠር ማሳሰባቸውና መስጋታቸው ተገቢና ሠላም ፈላጊው ሕዝብ ሁሉ የሚጋራው ነው። ይሁን እንጂ የፕሮግራሙ አላማ የግሉ ፕሬስ ሠላማዊ ዜጎች ሁሉ የሚጠሉትን ይሄን አደጋ ለማሣካትና ለማውረድ እኩይ የግል አላማቸውን ወይም የሚደግፉትን አቋም የሚያራምድ እና ወይም በገንዘብ የሚደግፉቸውን ቡድን አላማ ለማሣካት፣ ምንም ችግር ሣይኖር የግጭት አውራጅ ዘመቻ ያካሂዱ እንደነበር አፍራሽ ገፅታቸውን ማሣየት ነው። ለወደፊት ተመሣሣይ ችግር ውስጥ እንዳይገቡ ቢገቡም ሕዝብ ከባሕሪያቸው ይህን የግሉን ፕሬስ አካሄድ ተረድቶ በሠላም ሠርቶ የመኖር ፅኑ ፍላጎቱን ሊያሳጡት ከሚፈልጉ ወገኖች እንዲጠብቅ፣ ተደናብሮ ራሱንና አገሩን የሚጐዳ እርምጃ ለመውሰድ እንዳይነሳ ለማሳሰብም ነው። በእኔ እምነት አስተያየት ሰጪዋ "በቋፍ ያለ" ብለው የጠቀሱት ፤ የመገንጠል ጥያቄና ሌሎች የብሔር ብሔረሰብ መብት ጥያቄዎች በሕገመንግሥቱ ተገቢውን ምላሽ አግኝቷል። ምናልባት እነዚህ ጉዳዮች ላይ ጥርጣሬ ያላቸው ዜጐች ቢኖሩ፣ አብዛኞቹ እነዚሁ የግል ፕሬሶች የነዙት ውዥንብር ሰለባዎች መሆናቸውን በርግጠኝነት መናገር ይቻላል። ጋዜጦቹ ተከሰተ ወይም ይከሰታል ያሉት የሕዝብ ለሕዝብ ግጭት ያልነበረ የፈጠራ ወሬ መሆኑን እና የግጭት አውርድ ምልጃቸው ያለመሣካቱን ዛሬ ላይ ደርሰን በማየታችን አሁን እኩይ ገፅታቸውን በማስታወስ ያስጠነቅቃል እንጂ የነዙትን የመሰረተ ቢስ ሽብርና ስጋት ይዘን እንድንዘልቅ ያደርገን ዘንድ አይገባም ።

ነጋድራስ ጋዜጣም በዚሁ በኢቲቪ የቀረበ ፕሮግራም ላይ የተሰጡ አስተያየቶችን ጠቅሦ ዜና አስነብቦናል፡፡ እንደዜና ምንጩ ከአስተያየት ሰጪዎች መሀከል አንባቢ ያላት የአዲስ አድማስ ጋዜጣ ከፍተኛ አዘጋጅ የሆኑት ጋዜጠኛ ሠለሞን ገ/እግዚሃብሔርን መጥቀስ ወድጃለሁ፡፡ የወደድኩት ያለምክንያት አይደለም፣ ጋዜጣዋ ተነባቢ በመሆኗ ብዙዎች አስተያየቱን ከመቀበልና ካለመቀበል ፈተና ጋር ሊፋጠጡ ይችላሉ ብዬ ስለገመትኩ ነው፡፡

ኢቲቪ ባቀረበው የግሉን ፕሬስ የሚመለከት ጋዜጠኛ ሠለሞን ገ/እግዚአብሔር ለነጋድራስ በሰጡት አስተያየት፣ ፕሮግራሙ ሁለት ነገር እንደፈጠረባቸው ገልፀው "አንደኛው አሣፋሪ… ሆኖብኛል ሁለተኛው ደግሞ ያስፈራል" ነበር ያሉት፡፡ ይህንንም ሲያብራሩ "… የመንግስት ዕይታ እንዲህ ከሆነ የፕሬስ ነፃነት አደጋ ላይ ወድቋል፡፡ ማለት ነው፤ ምክንያቱም የፕሬስ ነፃነት የሁሉም መብቶች መገናኛ ነው ተብሎ ይታሰባል፣ ይህ መብት ከተሸራረፈ ሌሎች የዴሞክራሲ መብቶችም መስፋፋትና ማደግ አይችሉም፤ ያለችውን ትንሽ ዴሞክራሲ እንኳን ጠብቆ ማቆየት አይቻልም፡፡ የሚያሣፍረው ደግሞ የዩኒቨርሲቲ መምህራን እና የጋዜጠኛ ማህበር "ሊቀመንበር" ተብለው የቀረቡት ሠዎች፣ እንዲሁም ፕሮግራሙን ለማዘጋጀት የተሣተፉ በርካታ ጋዜጠኞች እንዲህ ከሆነ የሚያስቡት በዕውነት ያሣፍራል፡፡" ብለው፣ እንደምሣሌ የአዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ የሠፈረ "ቴሌ ቀውስ አጋጠመው" የሚል የዜና ርዕስ በቴሌቪዥን መስኮት መታየቱ ፕሮግራሙን በቡድን ያዘጋጁትን ጋዜጠኞች ሙያዊ ስብዕና ጥያቄ ውስጥ እንደሚከት ነግረውናል፡፡ ጋዜጠኛ ሠለሞን የአንጋፋዋና ተነባባዊ አዲስ አድማስ አዘጋጅ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በግሉ ፕሬስ ላይ ያቀረበውን ፕሮግራም አሣፋሪና አስፈሪ በማለት የፈጠረባቸውን ሁለት ስሜት የገለፀቡትን አስተያየት እንመልከት፡፡ ከፕሮግራሙ ላይ ተረዳሁት የሚሉት መንግስት በግሉ ሚዲያ ላይ ያለውን እይታ ነው፡፡ "የመንግስት እይታ እንዲህ ከሆነ፣ የፕሬስ ነፃነት የሁሉም መብቶች መገናኛ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ይህ መብት ከተሸረሸረ ሌሎች ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ማስፋፋትና ማሣዳግ አለመቻሉን" ነው አስፈሪ ያደርገዋል ያሉን፡፡ በተለይ ኢቲቪ ያስተላለፈውን ፕሮግራም ሳይመለከት ይህን የጋዜጠኛውን አስተያየት ያነበበ፣ ከመደናገር በስተቀር ከአስተያየቱ ምንም የሚረዳው ነገር የለም፡፡ ጋዜጠኛ ሠለሞን ስለየትኛው የመንግስት ዕይታ እንዳወሩ አልገለፁም፡፡ እርግጥ ነው የፕሬስ ነፃነት መሸራረፍ የለበትም፡፡ ሕገመንግሥቱም፣ የፕሬስ ሕግን ጨምሮ ሌሎች ከሕገመንግሥቱ የመነጩ ሕጐች ጥበቃ የሚያደርገውም ለዚህ ነው፡፡ እና ጋዜጠኛ ሠለሞን በፕሮግራሙ ላይ የተመለከቱት የትኛው የመንግስት ዕይታ ነው ይህን አሉታዊ ተፅእኖ የሚያስከትለው፣ የግል ፕሬሶች – አብዛኞቹ ባለፉት አመታት ለሕዝብ ሲያቀርቡ የቆዩት መሠረተ ቢስ አስፈሪ ዘገባዎችንና አስተያየቶችን ለሕዝብ በማስታወስ፣ ከግሉ ፕሬስ ያለፈ ታሪክ እንዲማር ማድረጉ ይሆን አስፈሪው? ጋዜጠኛው የፕሮግራሙን አሣፋሪነት ለማሳየት "የዩኒቨርሲቲ ምሁራን፣ የጋዜጠኛ ማህበር ፕሬዝዳንት እና ፕሮግሙን ለማዘጋጀት የተሣተፉት በርካታ ጋዜጠኞች የሚያስቡት እንዲህ ከሆነ …" ብለውናል፡፡ እንዴት የሚያስቡ ከሆነ? ጋዜጠኞቹ የግሉ ፕሬስ ሲያቀርብልን የነበረውን እንደወረደ ከማቅረብ ያለፈ የግል አስተያየታቸውን አልሰጡበትም፡፡

የዩኒቨርሲቲ ምሁራኑ በዘርፉ እንዳለ ባለሙያ ጥናቶችን ስለሠሩና ተማሪዎቻቸውን ጭምሮ በሌሎች አጥኚዎች ለተዘጋጁ ጥናቶች ቅርብ ስለሆኑ፣ እንዲሁም በዚሁ የፕሬስ ታሪክ ውስጥ ያለፉ በመሆናቸው በባለሙያ አይን የታዘቡትን ነው

የነገሩን፡፡ የጋዜጠኛ ማህበር ፕሬዝዳንት የተባለው፣ በዚሁ የፕሬስ ታሪክ ውስጥ በጋዜጠኝነት እየሠራ በማለፉ፣ እንዲያውም በአንድ ወቅት እርሱም በዚሁ ብልሹ የሙያ አሰራር ውስጥ ያለፈና ራሱንና ሙያውን በሂሳዊ እይታ ወደ ውስጥ ለማዬት የቻለ ጋዜጠኛ በመሆኑ ስለብልሹው አሰራር ከማንም በላይ ስለሚያውቅ ይህንኑ ያለፈበትን ልምዱን ነው ያካፈለን፡፡ እነዚህ አስተያየት ሠጪዎች ጋዜጦቹ ያልነበራቸውን በጎ ገፅታ "ነበራቸው" ብለው ዋሽተው አድናቆታቸውን መግለፅ ነበረባቸው? ፕሮግራሙን ያዘጋጁት ጋዜጠኞች የግሉን ፕሬስ ታሪክ ለመዳሰስ ባዘጋጁት ፕሮግራም ላይ ያልነበራቸውን አኩሪ ታሪክ "አላቸው" ብለው ማቅረብ ነበረባቸው? ወንጀላቸው ምኑ ላይ ነበር ? በአቶ ሰለሞን አዕምሮ አለማሰባቸው? ጋዜጠኛ ሠለሞን ለአሣፋሪነቱ ማረጋገጫ ያቀረቡት እርሳቸው ራሳቸው በሚያዘጋጁት ጋዜጣ — የአዲስ አድማስ የፊት ገፅ ላይ የሠፈረ "ቴሌ ቀውስ ኢጋጠመው" የሚል የዜና ርዕስ መታየቱን ነው፡፡ ሆኖም ግን ይህ ርዕሱ ከመታየቱ ባለፈ በዜናው ይዘት ላይ የተሰጠ አንዳችም አስተያየት አልነበረም፡፡ ይህ የጋዜጣዋ ዜና ርዕስ የቀረበው ፕሮራሙ የግሉን ፕሬስ የሚመለከት በመሆኑ፣ ቴሌቪዥን ደግሞ የዕይታ /visual/ ሚዲያ በመሆኑ፣ በግሉ ፕሬስ ታሪክ ውስጥ የነበሩትንና ያሉትን ጋዜጦች ምስል ማቅረብ ስለነበረበት ነው፡፡ አስተያየት ሰጪው ጋዜጠኛ ከፕሮግራሙ ተረዳሁት ያሉንና ያልገለፁልን "የመንግሥት ዕይታ" ያለችውን ትንሽ ዴሞክራሲ እንኳን ጠብቆ ማቆየት አያስችልም" ብለውናል፡፡ ይነቡብም አይነቡብም ያለአንዳች ስንክሳር ለአሥር ዓመታት ያለማቋረጥ በብዕር ስም መጨበጫ ውል በሌለውና ያለን ነገር በሙሉ በመቃወም( Nihilist) አባዜ የተቃኘ የግል አቋሙን ሲሸጠሽጥ የቆዬ ጋዜጠኛ እንደልቡ የሚያስበውን ለመፃፍ ፣የፃፈውንም ለማሰራጨት የቻለበትን ምህዳር "አንኳሶና አሳንሶ" "ጢኒጥ ዴሞክራሲ" ማለቱ ከማስተዘዛብ ያለፈ ፋይዳ አይኖረውም፡፡ በኢቴቪ ፕሮግራም በቀረበው የግል ጋዜጦች ብልሹ አሰራር ጥብቅና የቆሙት አቶ ሰለሞን በማንኛውም ነፃነት ሌሎች ተመሳሳይ ነፃነቶችን በማያስተጓጉል በሚጎዳና አፈፃፀማቸውን በሚያስቀር መንገድ መተግበር የሌለበት መሆኑን እንደማያውቁ ከአስተያዬታቸው መረዳት አያዳግትም፡፡ ይህን የሰብአዊ መብቶች አቡጊዳ መረዳት ያልቻሉና ብእር ስለጨበጠ ብቻ በሌሎች መሰረታዊ ህገ መንግስታዊ መብቶችና ነፃነቶች ኪሳራ የልቅና የመረን ነፃነት ሊቼንሳ የጨበጠ የሚመስለው ጋዜጠኛ ለጠቅላላ ማህበረሰቡ ብቻ ሳይሆን ቆሜለታለሁ ለሚለው ነፃነትም ጦሰኛ መሆኑን በጥቂቱ ተጨልፈው በኢቴቪ የቀረቡ ናሙናዎች ግሩም ማሳያዎች ናቸው ፡፡

በእኔ እምነት ለራሱና ለሙያው ክብር ያለው ማንኛውም ጋዜጠኛ ቢያንስ ቢያንስ የሙያውን ህዝባዊ አመኔታ ከፉኛ ከጎዱና ከሚጎዱ ብልሹ ምግባሮች ራሱን ማራቅ ብቻ ሳይሆን አሰራሮቹን በይፋ ለማጋለጥ የሚያስችለውን የሞራል ወኔ ማጣት ያለበት አይመስለኝም፡፡ አቶ ሰለሞን በማንትሴ "ሀ" እንደበት በየሳምንቱ የሚሰብኩት "የግለኝነት" አስተሳሰብም እንኳ ጎረቤትን ለመምሰል ብቻ በረድፍ ተኮልኩለው ያልተላመጠ የመንጋ አሳብን ከማራመድ በላይ የሚፀዬፉት ነገር ያለ አይመስለኝም፡፡ የብእር ስም ጭንብል ሲያጠልቁ "ድቅድቅ አምባገነናዊ" የሚሉትን ስርአት የአዘጋጅነት ቆብ አጥልቀው አደባባይ ሲወጡ "ትንሽ ዴሞክራሲ ያለበት" ነው ማለታቸው በርካታ ጥያቄን እንደሚያስነሳ እሙን ነው፡፡ ይህን በሌላ ርእስ በሌላ ፅሁፍ በስፋት ማየቱ የተሻለ ነው ብዬ ስለማምን ወደ ተነሳሁበት

ጉዳይ ልመለስ፡፡ ያለ ምንም ቅድመ ምርመራ፣ የሸዋና የወለጋ ነዋሪዎች እንኳን ይታዘቡናል ሳይሉ “ሸዋና ወለጋ በባሩድ ጭስ እየታጠኑ ነው” የሚልና መሰል ሰቅጣጭ ወሬዎችን እስከ ማውራት የተለጠጠ ነፃነትስ ትንሽ በሚሏት ዴሞክራሲ የተገኘ አይደለምን? እርግጥ ነው የሀገሪቱ ዴሞክራሲ መጐልበት ይቀረዋል፡፡ ይሁን እንጂ በፕሮግራሙ የቀረበው የግሉ ፕሬስ አካሄድ የሀገሪቱን ዴሞክራሲ መጥበብ ሳይሆን ፕሬሱ በዴሞክራሲያዊ ነፃነቱ መጠቀም ያለመቻሉን ነው የሚያሳየው፡፡ ዴሞክራሲ ህዝብን የማጫረስ፣ ሠላም የማደፍረስ ··· ነፃነትን አያስገኝምና፡፡